Abrham Yohanes https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No. 48.
ADDIS ABABA 5th July, 2018

**ማውጫ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፯/፪ሺ፲ ዓ.ም

የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ(ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .............ገጽ ፲ሺ፫፻፺፭

**Content**

Council of Ministers Regulation No. 427/2018

Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers (amendment) Regulation Page …………………………………….... 10395

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፯/፪ሺ፲

## የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፫፻፺፰/፪ሺ፱ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፯/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ማሻሻያ

የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፰/፪ሺ፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

Council of Ministers Regulation No. 427/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE AMENDEMENT THE FEDRAL HOUSING CORPORATION ESTABLISHEMENT REGULATION

**WHEREAS**, it is found necessary to amend the Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers Regulations;

**NOW THEREFORE,** this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic Ethiopian Proclamation No. 916/2015 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers (amendment) Regulation No.427/2018".

### 2. Amendment

The Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 398/2017 is hereby amended as follows:

Abrham Yohanes https://chilot.me



፩/ ከደንቡ አንቀጽ ፭ (፲፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (፲፬) ተጨምሮ፣ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) ንዑስ አንቀጽ (፲፭) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

"፲፬/ የሕንፃ ዕቃዎችን አምርቶ ወይም ገዝቶ ለቤት ግንባታ፣ ለጥገና፣ ለዕድሳት እና ለሌሎች ኮንስትራክሽን ሥራዎች አገልግሎት እንዲውሉ ማቅረብ፤"

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፤

"፮. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፴፫ ቢሊዮን ፩፻፷፭ ሚሊዮን ፮፻፸፬ ሺ ፩፻፴፮ (ሰላሳ ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፩ ቢሊዮን ፷፱ ሚሊዮን ፩፻፶፱ ሺ ፫፻፸፰ (አስራ አንድ ቢሊዮን ስልሣ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።"

፫/ ከደንቡ አንቀጽ ፰ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተጨምሮ ነባሮቹ አንቀጾች ፱ እና ፲ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፲ እና አንቀጽ ፲፩ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

"፱. <u>የተሻረ ሕግ</u>

የሕንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፬/፲፱፻፹፮ በዚህ ደንብ ተሽሯል።"

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተሸጋሸገው የደንቡ አንቀጽ ፲ ነባሩ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፤

1/ the following new sub-article (14) is added after Article 5 (13) of the Regulation and the existing sub-article (14) is renumbered as sub-article (15)

"14/ supply construction materials by manufacturing or through procurement so as to be used for house construction, repair and renewal and to be used for other construction works;"

2/ Article 6 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 6;

"6. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Corporation is Birr 33,165,674,136 (Thirty Three Billion One Hundred Sixty Five Million Six Hundred Seventy Four Thousand and One Hundred Thirty Six Birr) of which Birr 11,069,159,378 (Eleven Billion Sixty Nine Million One Hundred Fifty Nine Thousand Three Hundred Seventy Eight Birr) is paid up in cash and in kind.

3/ the following new Article 9 is added after Article 8 of the Regulation and the existing Articles 9 and 10 are renumbered as Articles 10 and 11 respectively;

"9. <u>Repealed law</u>

The Building Materials Supply Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 164/1994 is hereby repealed."

4/ As renumbered pursuant to sub-article (3) of this Article, the existing provision of Article 10 is numbered as sub-article (1) and the following new sub-article (2) is added:

Abrham Yohanes https://chilot.me



"፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፬/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የሕንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል።"

3. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

"2/ The rights and obligations of the Building Materials Supply Enterprise established under Regulation No. 164/1994 is hereby transferred to the Federal Housing Corporation.

3. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of July, 2018.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**